# ጀበናውና ከዳሚዋ

ከአብርሃም በየነ

የፌዝ ተቃዋሚ -ወገኗን አቂማ፣
ህዝቧን አስገብራ - ህይዎት ለከራማ፣
ጠላቷን ወዳጄ _ ፍቅረኛየ ስትል፣
ደረቷን በሎሚ - የመታት ይመስል፣
ወደድኩህ ስትለው፣
ወዳም ስትካድመው፣
የቡን ዐመልተኛ፣
አድርጓት ሱሰኛ፣
ስትል ደፋ ቀና፣
ይታዘቧትና፣
ስኒውን አትዘርጊ፣
አጉል አታዛጊ፣
የጀበና ቡና፣
እሳት ሲያየው ገና፣
ቱግ ቱግ ብሎ፣
ይደፋል ገንፍሎ፣
ቢሏት ችላ ብላ፣
ጀበና ወዘተች፣
ቡና ልታፈላ።
ጀበናውም ግሎ፣
ቡናውም ገንፍሎ፣
ሱሷን ሳያረካ፣
እንድትል አድርጎ፣ ይህም አለ ለካ፣
እንዳማራት ቀረ - ቶናና በረካ።
ከበረካው ሳይደርስ - ሥርዓቱ አብቅቷል፣
ጀበናው ተጥዶ - ስኒው ተዘርግቷል፣
መለስ ብላ ትየው - ጉልቻው ላይ ቀርቷል።

ግንቦት 2002